ጥቅምት 2006 (October – 2013)

**የአሲምባ ፍቅር**

**ደራሲ ካህሳይ አብርሀ (አማኑኤል)**

# ሽፈራዉ ላቀረበዉ ትችት መልስ

**በደራሲዉ - በካህሳይ አብርሀ (አማኑኤል) የቀረበ፤**

## 1. መግቢያ

ከሁሉ አስቀድሜ የአሲምባ ፍቅር የተሰኘዉን መጽሐፍ አሳትሜ ከጥቂት ወራት በፊት ለአንባብያን ካቀረብሁ በ ሁዋላ በመጽሐፉ ላይ በይፋ ድጋፍም ሆነ ነቀፋ ያዘሉ በርካታ ትችቶች በመቅረባቸዉ የተሰማኝን ልዩ የደስታ ስ ሜት በዚህ አጋጣሚ ለመግልጽ እወዳለሁ፤ መጽሐፉ ከጠበቅሁት በላይ ብዙ አንባብያንን ሊስብ በመቻሉ ከልብ እ ንድረካ አድርጎኛል፤ መጽሐፉን ባነበቡ፤ በሀገርም ዉስጥ ሆነ በዉጭ በሚገኙ ኢትዮጵያዉያን የቀረቡት ትችቶ ችና አስተያዮቶችም በጣም ገንቢና የሚያበረታቱ በመሆናችዉ የድካሜ ዉጤት ፍሬያማ በመሆኑ ከልብ ደስ እንዳለኝ በዘ ህ አጋጣሚ ለመግልጽ እወዳለሁ።

የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ ገና ከጅምሩ በህሊናየ ሲጠነሰስ በሩቁ ያየሁት ህልሜም ይህንኑ ነበር፤ መጽሐፌ በርካታ አንባብያንን አግኝቶልኝ ያ ከሞላ ጎደል ለአርባ አመት ያክል ተዳድፍኖና ተቀብሮ የኖረዉ፤ በኢሕፓ በተለይም በኢ ሕአሰ (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት) ስር ተሰልፈዉ ዉድ ሀገራቸዉን ኢትዮጵያን ከድህነት፤ ሁዋላ ቀርነትና እረሀብ፤ ግፍ ከሰፈነበት የአረመኔ የደርግ አገዛዝ ለማላቀቅና ነጻ ለማዉጣት ሲታገሉና ጠላታቸዉን በቆራጥነት ሲዋጉ ለ ተሰዉትና በየበረሀዉ፤ በየተራራዉ፤ በዱር በገደሉና በየሜዳዉ እየወደቁ ለቀሩት ጉዋዶች ማስታወሻ ብትሆን የአቅሜ ን ለማበርከት በሚል ነበር፤ መጽሐፉ በስፋት በተነበበ ቁጥርም ያ ህልሜ እየተሳካልኝ ለመሆኑ ምስክር ስለሆነ ደ ስታየ ወሰን የለዉም፤ የተመኘሁትም በመድረሱ በዚህ አጋጣሚ ለአንባብያን በሙሉ ከልብ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመጽሐፌ ዉስጥ እንደገለጽኩትም በዉድ ሀገራቸዉ ፍቅር ልባቸዉን ዉስጥ ለዉስጥ እየተቃጠሉ፤ በድህነቷና ሁ ዋላ ቀርነቷ እየተቆጩ፤ በጭቁን ሕዝቦቿ ላይ የሚደርሰዉ ከፍተኛ ግፍና በደል አንገብግቦአቸዉ፤ ገና በጮር ቃ እድሜአቸዉ በቁጭት ነደዉ፤ በትግል ተሰማርተዉ አረመኔዉን ጠላት ለመጣል በቆራጥነት ሲዋጉ፤ በየመንገዱ፤ በ ዱር በገደሉ ለወደቁት ጀግኖች ጓዶች ምሳሌ እንዲሆኑ በሚል እኔ በተሰማራሁባቸዉ የሰራዊት ሀይሎች፤ ክፍልታ ትና የጦር ሜዳወች አብረኤቸዉ ከጎናቸዉ በመሰለፍ ፈታኙን የትግል እሳት ግርፊያ ስቀበል፤ ከጎኔ ተለይተዉኝ የ ወደቁትን ሁሉ አንዳቸዉንም በዘርም ሆነ በጎሳ በሀይማኖት ወይም በጅኦግራፊ ሳልለይ፤ የማስታዉሰዉን በሙሉ የ ትግሉን ምሬት፤ ስእሉንና ታሪኩን በምችለዉ አቅም መጠን ለማቅረብ ሞክሬአለሁ። በእድልና በታምር ከዚያ እሳ ት ተርፌም እድሜ ሰጥቶኝ፤ ለእነዚህ ቆራጥ ጀግና ጓዶች መታሰቢያ ብትሆን በሚል የአቅሜን ጽሁፍ ለማበርከት ቆርጬ ተነስቸ ያሰብኩትን ህልሜን ለማሳካት የረዱኝን በቅድሚያ ፈጣሪየን ቀጥየም ይህን መጽሐፍ እንዳወጣ የተባበሩ ኝን በሙሉ፤ ቅን ወዳጆችን፤ የትግል አጋር ጓዶችን፤ ቤተሰቦቸንና ሌሎች ንም በርካታ ሰወች እንዲሁም የመጽሐፌን አ ንባቢያን አሁንም እንደገና በዚህ አጋጣሚ ከልቤ አመሰግናለሁ።

የአሲምባ ፍቅርን መጽሐፍ ጽፌ ለአንባብያን ወይም ለሕዝብ ሳቀርብ ከሁሉም መልካም ትችት አገኛለሁ የሚል የ ተሳሳተ ግምትም አልነበረኝም፤ እንደዚያ ባስብ የዋህነት ይሆናልና፤ ሊኖረኝም አይችልም፤ አንድ ሰዉ የሆነ ትል ቅ ሊባል የሚችል አርእስት ያለዉ የጽሁፍ ፕሮጀክት አስቦ ከተነሳ ወይም ግቡ ከተሳካለት፤ ወይም የ በርካታ አንባቢንና አዳማጭን ቀልብ የሚስብ ጽሁፍ ካወጣ በተለይም በእኛ ኢትዮጵያዉያን መካከል ደጋፊና ወ ዳጅ ብቻ ሳይሆን ከታሰበም ሆነ ካልታሰበ አቅጣጫ ደጋፊ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ ወይም ከባሰ ጠላትም ሊያፈራ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም፤ አንዳንዶችም አጋጣሚዉን በመጠቀም እራሳቸዉን ለማስተዋወ

ቅ ሌላዉ በዋለበት ሜዳ ላይ የነፃ ፈረስ ለመጋለብ የሚሻኮቱ እንደሚኖሩ ያለ ሀቅ ነዉ፡፡

ይህን ስል በመጽሐፉ በሀቅ ላይ የተመሰረተና ቅንነት የሞላበት ገንቢ ትችትና አስተያየት (የጻፍኩትን ታሪክ የሚደግፍ ም ሆነ የሚነቅፍ ወይም የሚቃወም) የሰጡኝን አንባብያን በሙሉ አሁንም ከልቤ እያመሰገንሁ ግን ሆነ ብለዉ ያላ ሰብኩትንና በመጽሐፉ ዉስጥ ያላካተትኩትን እየጨማመሩ፤ ልዩ ትርጉም በመስጠት፤ ድካሜን ዋጋ ለማሳጣትና መጽሐፉን ለማጣጣል፤ ከዚያም አልፎ የእኔን የትግል ታሪክ በማሳነስ፤ እኔን የመንፈስ ደካማና ፈሪ እንደነበርኩ ለ ማስመሰል ዝቅ በማድረግ፤ እራሳቸዉን ግን አዋቂና የትግል አርበኞች በማስመሰል ስማቸዉን ላይ ለመስቀል የሚ ሞክሩትን የለም ይህማ አይሆንም እላለሁ፤ ደግነ ቱ የሁለታችንንም፤ የእነዚህንም ግለሰቦች ሆነ የእኔን የትግል ተሞክ ሮና ታሪክ፤ ባህሪና የቆራጥነት መንፈስ፤ በሚገባ ጠ ንቅቀው የሚያቁና፤ በትግል ተሞክሯቸው በበርካታ ጓዶች የሚ ከበሩና የሚታፈሩ ስላሉ ፍርዱን ለእነሱና ለታሪክ እየሰጠሁ የሚደርስብኝን አጉል ዘለፋ እየናቅሁ አልፈዋለሁ፤ ስለዚህ አጉል ዘለፋዉ ቅንጣትም አይረብሸኝም፡፡

ብዙወቻችን ባሳለፍነዉ መራራ የትግል ታሪክ ዉስጥ ስንት ከዚህ የባሰ ፈተና ስላሳለፍን ይህ አዲስ ነገር አይሆንብኝም፤ በአጋጣሚ በህይወት የተረፍን በርካታ ጓዶች ከመራራዉ ትግል የወረስነዉ ትልቅ ቅርስ ቢኖር የመንፈስ ቆራጥነት ንና ቅንነትን ሀቀኝነትን ነዉ፤ ይሁን እንጅ አንዳንዶቹ ደካሞች ይህንም መልካም ቅርስ እንኳን በትግል ለወደቁት ጓዶች ማስታወሻ ቢሆን ለማቆየት የሚሳናቸዉ አሉ፤ በተለያዩ ዘመንና አካባቢ በወለዳቸዉ ተልካሻና እርካሽ ጥቅሞች በመገዛት፤ ከስንት ፈተና ተርፎ ለታሪክ የቀረዉን መልካም የኢሐፓ/ሰ ጓዶች ቅርስ ሲያጣምሙ ወይም ለእራሳቸ ዉ መኖሪያ ለማድረግ የሚሞክሩ አይታጡም፤ ይህን ማየት በህይወት ቆመን ላለነዉ የድሮ ኢሕአፓ/ሰ ጓዶች በ ጣም ያሳዝናል፤ ለዉጭ ታዛቢም አሁንም እነዚህ ሰወች ከመነታረክና ከጠላትነት ስሜት ከመከፋፈል አልዳኑም ማለት ነዉ የሚል ስም ሊያሰጠን ይችላል፤ በሀገራቸዉ ፍቅር ነደዉ፤ ጠላትን በቆራጥነት ሲታገሉ በወደቁት የኢሐፓ /ሰ ጓዶች የትግል ታሪክ ላይም ጥላሸት ሊጥል ይችላል፡፡

## 2. ምስጋናና ማበረታቻ ለሽፈራዉ፤

ሽፈራዉ ስለጻፈዉ ዝርዝር የአሉታ ትችት አንድ በአንድ መልስ ከመስጠቴ በፊት በቅድሚያ ለእሱም ቢሆን በ ተለይ ያለኝን ምስጋና ማሳወቅ እፈልጋለሁ፤ በጽሁፉ መጨረሻ ላይ እንደገለጸዉ፤

"የአማኑኤል "የአሲምባ ፍቅር" በመዉጣቱ ብዙወቻችን እዉነተኛ የኢሕአሰን ታሪክ እንድንጽፍ ማበረታታት ብቻ ሳይሆን በታሪክ ተ ጠያቂነታችንን እንድናስብ ይመረምራል፡፡ ከብዙ ጉዋዲቶችና ጉዋዶች ጋር እንድንወያይበትም ምክንያት ስለሆነ በዚህ አማኑኤልን አመሰግነዋለሁ፡፡ እኔም ሆነ ሌሎች በትግሉ ያለፍን እዉነተኛዉን ታሪክ በመጻፍ ለትዉልድ ማስተላለፍ ሀላፊነት አለብን፡፡ ሁላችን ም የምናዉቀዉን ሀቁን ለመናገር፤ ለመጻፍ ለማቅረብ፤ በዉይይት መካፈል ይገባናል እላለሁ፡፡" ይላል ሽፈራዉ፡፡

በእዉነቱ ሽፈራዉ ይህን አምነህ በመቀበልህ በጣም አመሰግንሀለሁ፤ እዉነትም አንተ ይህን ካልህ አንዱ ዋነኛ ህልሜ ተሳክቶልኛል ማለት ነዉ፤ አኔም መጽሀፌን ስጽፍ አንዱ ዋናዉ የተመኘሁት እሱኑ ነበር፤ እኔ በህይወት ተርፌ እዚህ ከደረስኩ አይቀር የአቅሜን የማቀዉን ወይም የማስታዉሰዉን በትግል የወደቁ የኢሐፓ ጓዶቸን ታሪክ በጽሑፍ ባቀርብ፤ ምናልባት ሌሎችንም ከእኔ የተሻለ ተሞክሮና የጽሁፍ ችሎታ ያላቸዉን ጭምር እንዲጽፉ ላነ ቃቃና ላበረታታ እችል ይሆናል ብየ በማለም ነበር፤ አንተም ሞራልክን ከፍ አድርገህ ለመጻፍ መነሳት አለብን እያልክ ስታነቃቃ መስማት ለእኔ ልዩ ኩራት እንዲሰማኝ አደርገኸኛል፡፡

ከመጻፍም አልፈህ ጓዶች እንዲወያዩ በመጋበዝህ ሳላመሰግንህ አላልፍም፤ የአንተም ህልምህ ተሳክቶልህ፤ ብርታቱ ን ሰጥቶህ መጽሐፍክን ጨርሰህ ለአንባብያን አቅርበህ እንድናይህ ከልቤ እመኝልሀለሁ፤ መጽሐፍክን ለማንበብም በጉጉ ት እጠባበቃለሁ፤ ይቅናህ፤ ከዚያም አልፎ በትችትህ ላይ በተደጋጋሚ እንደገለጽከዉ መጽሐፌን ስጽፍ በምክር ከማ በረታታት አልፈህ፤ ታትሞ ከወጣም በሁዋላ ለአንባብያን በማስተዋወቅና በማሰራጨትም ስላገዝከኝ አመሰግንሀለ ሁ፤ በእኔ አካባቢ ላሉት አንባብያን ልሽጥልህ ብለህ 50 የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ በመውሰድህም ከልብ ሳላመሰ ግንህ ማለፍ አልፈልግም፤ እስካሁንም መጽሐፉ ተሽጦ አልቆ ይሆናል የሚልም ግምት አለኝ፡፡

አሁን ይቅርታ አድርግልኝና ወድትችትህ መልስ መስጠት ላተኩር።

## 3. ለሽ ፈራዉ በአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ ላይ ትች ቶች መ ልስ በዝርዝ ር፤

### ሀ) ስለእኔ ከኢሐፓ ድርጅ ት ለቆ ወደ ኤርትራ መግ ባ ት፤

ሽፈራዉ ደግሞ ደጋግሞ “የትግራይ ጉዋዶች“ እያለ በትችቱ ዉስጥ የሚያነሳዉ በመሰረቱ የቃላት ግድፈት ሳይሆ ን አሁንም የትምክህተኝነትና በጠባብነት የተመረዘ የአንድ ሕዝብ ጥላቻ ሁዋላ ቀር አስተሳስብ ችግር በህሊናዉ እን ዳላበት ነጸብራቅ ነዉ የሚል እምነት አለኝ፤ በኢሐፓ ዉስጥ በጊዜው የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ነጣጥሎ በማየት “የትግራይ ጓዶች” “የአማራ ጓዶች” “የኦሮሞ ጓዶች” ማለት የተለመደ አልነበረም፤ የሽፈራዉ አይነቶቹ ጥቂት ትምክህተ ኞችና ሁዋላ ቀሮች ግን በተለይም ወደመጨረሻ አካባቢ ኢህአሰ ሊፈርስ ሲቃረብ “የትግራይ ጓዶች” እያሉ እየለዩ ማጥላላትና ስም ማጥፋት አዘዉትረዉ ነበር ቢባል ከእዉነት የራቀ አይደለም እላለሁ፤ ሽፈራዉም የዚያ ርዝራዥ ሁዋ ላ ቀርና ከፋፋይ ጠባብ አስተሳሰብ አሁንም ከህሊናዉ እንዳልወጣለት ከትችቱ በግልጽ ይታያል፤ የሚገርመዉ ሽ ፈራዉ “የትግራይ ጓዶች” ፈሪና ከሀዲ እንደነበሩና ለኢሀሰ መፍረስም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ አፉን ሞልቶ በትችቱ የሚናገረዉ ነዉ፤ ይህ መችም ከፍተኛ የታሪክ ማዛባት ሴራና ዘረኝነት የሞላበት ጥላቻና ልክፍት አሁንም ህሊናዉን እንደተጠናወተዉ ያሳያል ከማለት አልፌ ምን ልል እንደምችል ግራ ይገባኛል፤ ከዚያም አልፎ እነዚህ የፈረደባቸዉ ሽፈራዉ የትግል ታሪካቸዉን የሚያጥላላቸዉ የኢሐፓ/ሰ ጓዶች በተለይም የትግራይ ተወላጆች “የወ ያኔ ተባባሪወች” ነበሩ ብሎ ማቅረብ የሚያሳዝን ነዉ፤ ሽፈራዉ ምነው በወደቁ ጓዶች ግፍ ባትናገር!

ትክክለኛዉን ታሪክ በአጭሩ ለአንባብያን ለማቅረብ እሞክራለሁ፤ ኢሕአፓ/ስ የትጥቅ ትግል ሲጀምር ገና ትን ሽ እያለ በርካታ የትግራይ ተወላጆች ቦታዉ ስላመቻቸላቸዉና በዐላማዉም ስላመኑ (እኔን ጨምሮ ማለት ነዉ) ሰራዊቱን ተቀላቀልን፤ በመጽሐፌ ዉስጥ እንዳካተትኩትም በርካታ የትግራይ ተወላጅ ጓዶች ከሌሎችም ብሔረስቦ ች ከመጡ ጓዶች ጋር ገና በኢሀሰ ጮርቃነት ጊ ዜ ጀምረዉ ከጠላት ጋር በግንባር ቀደም በቆራጥነት ሲዋጉ ተሰዉ ተዋል፤ ይሁን እንጅ ያኔ በግልጽ እንደታየዉ ምናልባትም ከሌላ አካባቢ ከመጡ ጓዶች በበለጠ ከሕወሀት (ሕዝባዊ ሐ ርነት ትግራይ) የሚቃጣ ትልቅ ፈተና የገጠማቸዉ በኢሐሰ ዉስጥ የተሰለፉ የትግራይ ተወላጆች እንደነበሩ ታሪክ ሊፍቀዉ የማይችል ሐቅነዉ፤ እናንተ ሕዝባችሁንና ሀገራችሁን (ትግራይን ማለት ነዉ) የሸጣችሁ የአማራ ኩራኩ ሮችና ከሀዲወች አደርባዮች ናችሁ እየተባሉ በሕወሀት ታጋዮች የሚሰነዘርባቸዉን በትር በአንድ በኩል ለመቋቋም ሲታገሉ፤ እንደሽፈራዉ አይነቶቹ በሰራዊቱ ዉስጥ ያሉ ጥቂት ትምክህተኞች ደግሞ በተለይም በኢሐፓ/ስ ና ሕወሀት መካከል የተቀሰቀሰው ዉጊያ እየተፋፋመ ሲሄድ እነዚህ የሕወሀት ወኪሎችና ሰላዮች ናቸዉ እያሉ ሞራል የሚጥል ዝ ልፊያ መስጠት እየተከሰተ ነበር።

የሚገርመዉ ገና ኢሕአሰ በመጠናከር ላይ እያለ ከሕወሀት ጋር በትግራይ መሬት ሽኩቻ ሲካሄድ ትልቁን ፈተናና ገፈ ት ግንባር ቀደም በመሆን የሚቀበሉት የነበሩም በርካታወቹ እነዚህ በኢሀሰ ዉስጥ በተለይም በጋንታና በሀይል አመ ራር ሀላፊነት የነበሩ የትግራይ ተወላጆች እንደነበሩ እያወቀ ሽፈራዉ የነዚህን ጓዶች የትግል ታሪክ ለማጥፋት ዘ መቻ መክፈቱ ነዉ፤ ብዙወቹም ገና ሽኩቻዉ ሲጀመር አንስቶ በሁዋላም በእርስበርስ ውጊያዉ በቆራጥነት ለኢሐሰ ሲዋጉ ህይወታቸዉ አልፏል፤ ሽፈራዉ ይህን ሁሉ እያወቀ ነዉ እንግዲህ “የትግራይ ጓዶች” ላይ ያለዉን ጥላቻ ለመግለጽ ሲ ል የእነዚህን ቆራጥ ጓዶች ብቻ ሳይሆን የኢሐሰንም ታሪክ አብሮ ጥላሸት የሚጥልበትና የሚያበላሸዉ፤ ምናለበት ሀ ቁን ተናግረህ ብትሞት! ለየትኛዉ ዐለም ብለህ ነዉ የምትዋሸዉ?

በቅድሚያ በወቅቱ በኢሐፓ/ኢህአሰ ላይ በደረሰዉ የዉስጥና የዉጭ ቀዉሶች ወይም ችግሮች የተነሳ (ዋና ዋናወቹን ለ መጥቀስ፤ “የእርማት እንቅስቃሴ” “የአንጃ ጥያቄ” ከህወሀት ጋር ግጭትና ጦርነት፤ ድርጅቱ በሞራልና ዲስፕሊን መ

ዳከምና መፈረካከስ ሲጀምር በየአቅጣጫዉ በርካታ ጓዋዶች በሚችሉት ሁሉ መንገድ እየጠፉ መሄድ እንደቀጠሉ ታሪክ የማይረሳዉ ነዉ፤ እነዚህም ጓዶች የትግራይ ተወላጆች ብቻ እንዳልነበሩ ግልጽ ነበር፤ ምናልባትምየ ትግራይ ተወላጆች ከሌሎች የሚለዩበት አካባቢዉን ስለሚያቁት ወይ ም መንገድ ለማመቻቸት የተሻለ እድል ስለነ በራቸዉ በቀላሉ መጥፋት መቻላቸዉ ብቻ ነዉ እንጅ፤ ከሌሎቹ በተለየ ወኔ የማጣት ወይም ሰራዊቱን የመክዳ ት ስሜት ስለነበራቸዉ አይደለም።

ሽፈራዉ ለመሸፋፈን የሚጥረዉ የኢሐፓን ድርጅት በድንገት እንደናዳ እንዲፈርስና እንዲፈረካከስ ያበቁትን ምክን ያቶች ነዉ፤ እኔንስ እሽ ከዳተኛ በለኝ አንተስ ምን ነካህ ታዲያ? ለምን ወደኤርትራ ገባህ? በአጭሩ ለምን የኢሐፓ ሰ ራዊት (ኢሕአሰ) ከፍተኛ አመራር ጉዋዙን ጠቅሎ፤ የሚገድለዉን ገድሎ፤ የሚቀብረዉን ቀብሮ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ጓ ዶችን እየመራ እኔ በለቀቅሁ በጥቂት ቀናት ዉስጥ ወደኤርትራ አፈገፈገ? እንደሽፈራዉ ትንታኔ መሰረት በ“ትግ ራይ ጓዶች” ወኔ ማጣትና መክዳት ምክንያት ነዉ ሰራዊቱ የተበታተነዉና የፈረሰዉ!! ሽፈራዉ እዉነትም ትክክሉን የኢሐፓ ታሪክ ለመጻፍ ብቁ መሆንክን እያሳየህ ነው! ይቅናህ ሌላ ምን እላለሁ።

በነገራችን ላይ ከኤርትራ ተነስተን ሱዳን ስንገባ ክእኔ ጋር ብቻ 75 የሚሆኑ ጓዶች ነበሩ፤ ከእነዚህም ጓዶች እኔ እስከ ማስታዉሰዉ ድረስ “የትግራይ ተወላጅ የኢሀአሰ ጓዶች” በእጣት የሚቆጠሩ ነበሩ ማለት ይቻላል፤ አብዛኞቹ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች የተመለመሉ ናቸዉ፤ እዚህ ላይ እንደምሳሌ ብጠቅስ አሁን “የግንቦት 7” መሪና መስራች ነኝ የሚለ ዉ ' ዶክተር ብርሀኑ ነጋም ወደ ሱዳን ስንሰደድ አብሮን እንደነበር ነዉ፤ ሽፈራዉ እሱንም የትግራይ ተወላጅ ነዉ ካላለ በስተቀር!

## ለ) ስ ለወሎ ኦፐሬሽን፤

ሽፈራዉ በትክክል እንዳለዉ የወሎ ኦፐሬሽን በኢህሰ የትግል ታሪክ ዉስጥ ትልቅ ስፍራ መያዝ የሚገባዉ ነዉ ብ የ አምናለሁ፤ ለምን ቢሉ ይህ ከፍተኛ ዉድቀት ያስከተለ ወታደራዊ ኦፐሬሽን ምናልባትም ለአዲሱ ትዉልድ በ ተለይም የትግል መሪ ፓርቲና በስሩ የሚመራዉ የትጥቅ ትግል ሰራዊትን ዉስብስብ ግንኙነቶች ለመረዳት ለሚ ፈልጉ እንደምሳሌ በመሆን ይረዳ ይሆናል ብየ በመገመት ነዉ፤ ቀጥየም የአቅሜን በአጭሩ ለማብራራት እሞክ ራለሁ፤ ምናልባትም ለወደፊቱ ከእኔ የተሻለ የትግል ተሞክሮ ያላቸዉና በተለይም በወቅቱ በከፍተኛ አመራር ሀላ ፊነት ላይ የነበሩና በእድል ከመሰዋት ተርፈዉ በህይወት ያሉ ጥቂት የኢሀሰ ጓዶች ይጽፉታል ብየ ተስፋ አደርጋ ለሁ፤ ሽፈራዉም በኦፐሬሽኑ ተካፍሎ ስለነበር እጽፋለሁ በሚለዉ መጽሐፉ እኔ የረሳሁትም ካለ እሱንም አካቶ በሚገ ባ እንዲገልጸዉ ከልቤ እመኝለታለሁ።

የወሎ የኢሀሰ ዘመቻ ገና ከጅምሩ ሲጠነሰስና ሲወሰን እንዲወድቅና እንዳይሳካ ያደረገዉ የኢሀፓ ከፍተኛ አመራር (የፓርቲዉ ማእከላዊ ኮሚቴ ልኡክ ነን ሲሉ የነበሩት) የተሞክሮ እጥረት፤ ጠባብና ዉሱን ወታደራዊና የፖለቲካ ስትራቴጅ ዉጥን እንደነበር ከኢሀሰ ታሪክ ለመረዳት ይቻላል፤ ከፍተኛ የወታደራዊ አመራር ተሞክሮና እዉቀት ያላቸዉ የሰራዊቱ የበላይ አመራሮች (የፓርቲዉ ማእከላዊ ኮሚቴ ሳይሆን) ይህን የወሎ ዘመቻ ገና ሰራዊቱ ባልዳበረበትና አቅም በሌለዉ ወቅት ማድረግ ትክክል እንዳልሆነና፤ እልቂትም ሊያስከትል እንደሚችል በጥብቅ ቢቃወሙም የፓርቲዉ ማእከላዊ ኮሚ ቴና ፖሊትቢሮ አመራር ተወካዮች ነን ባዮች (“ልኡክ”) አይሆንም ሰራዊቱ ወሎ መግባት አለበት ብለዉ ድርቅ አሉ፤ በ ዚህም ዘመቻ ምክንያት ያ ሁሉ ዉድቀት ሊደርስ ቻለ፤ ይህን ደግሞ አሁን በህይወት ያሉት የሰራዊቱ ከፍተኛ አመራ ር አባላት ሊመሰክሩ ይችላሉ።

የፓርቲ የበላይነትን ማክበር በሚል መተከል የሰራዊቱ ከፍተኛ አመራሮችንም ሀሳብና ተቃዉሞ የፓርቲዉ የበላ ይ አካላት ባለመቀበላቸዉ ያን የመሰለ ትልቅ ስህተትና አደገኛ ዉሳኔ ያስከተለዉን ከፍተኛ ውድቀትና መዘዝም ሁሉም የሚያቀዉና ታሪክ የመዘገበዉ ነዉ፤ ገና በድርጅትና በወታደራዊ አቋም በትጥቅም ያልዳበረን ሰራዊት ሰ ነጣጥቆ ጠላት በተጠናከረበትና፤ ሕዝቡም ባልነቃና ባልተደራጀበት አካባቢ ጥቂት ጓዶችን ጠላት ጉያ ስር እሩቅ በ

ታ ልኮ ማስጨረስ ከጀብደኝነት አልፎ ትልቅ ወታደራዊ ስህተት እንደነበር በትጥቅ ትግል ተሞክሮ ያላቸዉ ሁሉ ሊገነ
ዘቡት የሚችሉ ሐቅ ነዉ፣ የኢሐፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባሎች ነን የሚሉ ግን በተደጋጋሚ የፓርቲ የበላይነት በሚል
ፈሊጥ ይህን የመሰለ ከፍተኛ ስህተት በመስራት ሰራዊቱ እንዲዳከምና በሁዋላም በተለያየ አቅጣጫ የተቀነባበረ ጥ
ቃት ሲደርስበት ለመቋቋም አቅም አጥሮት ለመፍረስ እንዲበቃ ከፍትኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፣ የኢሐፓ ማእከላዊ
ኮሚቴ አመራር ተወካዮች ነን የሚሉ የሰሯቸዉ ከባድ ስህተቶች በወታደራዊ ስትራቴጅ ብቻ አይወሰኑም፣ ለሰራዊ
ቱ መፍረስ ሌሎችም አይነተኛ መንስኤወች ነበሩ፣ ከእነዚህም ዉስጥ “የእርማት እንቅስቃሴንና የአንጃን ጥያቄውች” መ
ጥቀስ ይቻላል፣ እንዚ ህንም ምናልባት ለወደፊቱ የሚጽፉ ከእኔ በተሻለም ሊተነትኑ የሚችሉ ጓዶች ይመጡ ይሆና
ል የሚል ተስፋ አለኝ፣ ይህን ከወሎ ዘመቻ ጋር የሚያያዝ አስፈላጊ ማብራሪያ ከሰጠሁ በሁዋላ አሁን ወደአሲምባ
ፍቅርና ወደ ሽፈራዉ ትችት ልመለስ።

ሽፈራዉ የኢሐፓ አመራር ከወሎ ስህትቱ እራሱን ገምግሞ ተምሯል፣ አንተ ነህ እንጅ ስሙን የምታጠፋዉ በሚል
ይወነጅለኛል! እንደእዉነቱ ከሆን ግን ኢህአፓ ከስህተቱ ቢማር ኖሮ ከወሎ ኦፐሬሽን በሁዋላ ሽፈራዉ አንተ እራስህ
የሀይል ኮሚሳር የነበርክባት ሀይል ሶስት ከትግራይ ተነስታ አገር አቋርጣ፣ ቤገምድር ገብታ ይባስ ብሎ በለሳ ድረስ ዘ
ልቃ ሄዳ ያለአቅሟ ከጠላት ጋር ተልካሻ ጦርነት ከፍታ ስንትና ስንት በቀላሉ ሊትኩ የማይችሉ ቆራጥ ቆራጥ ጓዶችን
ባላጣን ነበር።

በነገራችን ላይ አንተም በወሎ እልቂት ላይ አልፈህና ያንን ከፍተኛ ወታደራዊ ስህተት ሲፈጸም ታዝበህ መጥተህ
ትምህርት ሳታገኝ መቅረትህ ያሳዝናል፣ ሀይል ሶስትን እየመራህ በበለሳ ጦርነት ያልታዘዝከዉን ከሀይል መሪዉ ከ
ሀይሌ ቀጭኑ ጋር ወስነህ ያላቅሟ በተልካሻ ወታደራዊ ስትራቴጅ እየተመራች ከጠላት ጋር በጦርነት እሳት እ
ንድትማገድና ጓዶች እንዲያልቁ አድርገሀል፣ ይህን የሀይል ሶስት ኦፐሬሽን ደግሞ የኢሀሰ ታሪክ ሊረሳዉ የማይ
ችል ተሞክሮ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፣ በዚህም ከሀይል መሪዉ ከሀይሌ ቀጭኑ ጋር ሆነህ በፈፀምከው ከባድ የወታደራዊ
ና ፖለቲካዊ ስትራቴጅ ስህተት በወታደራዊ ትሪቡናል ክስ ቀርቦብህ፣ ከሀይል ኮሚሳር ሀላፊነትህ ስልጣን ወርደህ፣ ለስ
ድስት ወር ብረትክን እንድታወርድ ተወስኖብህ እንደነበር የማይረሳ ሀቅ ነዉ፣ ከዚያ በሁዋላም እንኳን በዉጊያ ገብተህ
ጀብዱ ልትሰራ ቀርቶ ለረዥም ጊዜ የጋንታ ስንቅ ቀረጢት፣ አልዚያም ግፋ ቢል ብረት የሌለዉ ጥይት እየተሸከምክ ስ
ትዞር እንደነበር ያኔ ኢህአሰ ዉስጥ የነበሩ ሁሉም ጓዶች የሚያቁትትና ፈጽሞ ሊረሳ የማይችል የጎላ ሀቅና ታሪክ ነዉ።

ጓድ ሽፈራዉ በወሎ ጦርነት ስለጓድ አሊጋዝ መሰዋት ምክንያቶችና ሁኔታወችን በአሲምባ ፍቅር መጽሐፍህ በሚ
ገባ አላካተትክም በሚል ትነቅፈኛለህ፣ ምን አድርግ እንደምትለኝ እልገባኝም፣ ፍርዱን ለአንባብያን እተወዋለሁ፣
ጓድ እሊጋዝ ሲመታና ሲወድቅ በሩቁ አየሁ ማለት ምኑ ሀሰት እንደሚሆን አልገባኝም፣ ምናልባትም አንተ ሽፈራ
ዉ አብረህ ከአሊጋዝ ጋር እንደነበርክና በቆራጥነት ተዋግተህ ከሞት እንደተረፍክ ብየ ስለአንተ የማላቀዉን ሁሉ
ታሪክና ጀብዱ ጨማምሬ አሳምሬ ለምን በመጽሀፍህ አላካተትክም ብለህ አኩርፈህ ከሆነ ይህን ያክል የምታወግዘኝ
ይቅርታ አድርግልኝና ያ ትክክል አይሆንም ነበር፣ በመጽሐፌ የማንንም የሌለ ዝና ከእራሴ ጀምሮ አላካተትኩም፣ የአ
ንተ ከእሊጋዝ ጋር አብሮ መኖርና ከገበሬዎች ጋር በቆራጥነት መዋጋትህ ሆኖም ከሆነ በእእምሮየ ስላልመጣልኝ
እንጅ ሆነ ብየ የአንተን ታሪክና ጀብዱ ለማጣጣል ያደረግሁት ተንኮልም እንዳልሆነ እንድታዉቅልኝ እፈልጋለ
ሁ፣ አንተ መጽሀፍክን ስትጽፍ እኔ የረሳሁትን ታሪክህንና ዝናህን በሚገባ እንደምትገልፀዉም ተስፋ አለኝ፣ እንዳል
ኩህም መጽሐፍክን ለማንበብ በጉጉት እጠብቃለሁ።

ከዚያ በተረፈ ግን ስለወሎ ዘመቻ ዉድቀት የኢህፓ ከፍተኛ አመራር የመጀመሪያ ኮንግሬሱ ላይ ተወያይቶበታ
ል፣ ይህን ደግሞ አበበ ደብተራዉም ነግሮናል ለምትለዉ ምን ማለት እችላለሁ፣ የኢህፓ ከፍተኛ እመራር ወይም
“ፓርቲዉ” ያቃል ተነጋግሮበታል የሚል ስንት ነገር ተነግሮናል፣ ጓድ ሽፈራዉ እሱ አይደለም ዋናዉ ቁም ነገር፣ እኔ
እንደሚገባኝ ከሆነ ዋናዉ የፓርቲዉ መመዘኛ ተግባሩ እንጅ ወሬዉ አይደለም፣ የኢህአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አመራር
ወይም ፖሊትቢሮ አባልና ልኡክ ነን የሚሉት ጥቂት ግለሰቦች በኢህአሰ ላይ በተደጋጋሚ የፈጸሙዋቸዉን ትላልቅ
ስህተቶችና ደባወች በዚች ትንሽ ጽሁፍ ወይም በአሲምባ ፍቅር ጽፎ ለመጨረስ የሚቻልም አይመስለኝም፣ አቅ

ሙም ስለሌለኝ ለሌሎች እተወዋለሁ፤ አንተ አቅሙ ካለህ በጽሁፍህ በትክክል ብታሰፍረዉና ብታቀርበዉ ደስታዉ
ንም አልችለዉ፤ እዉነትም የታሪክ ግዴታህን ከእኔ በበለጠ እንደተወጣህ እቆጥረዋለሁ።

## ሐ) ስለዉቅሮ ኦፐሬሽን፤

ስለዚህ ኦፐሬሽን ዝርዝር መልስ ለሽፈራዉ ትችት ከማቅረቤ በፊት ለአንባብያን ማስረዳት የምፈልገዉ አንድ ነገር
አለ፤ ይኸዉም ይህ ተሞክሮም እንደገና ከፍተኛ እልቂት በጓዶች ላይ ያደረሰና በቆራጥነታቸዉና ጀግንነታቸዉ፤
በሀገርና የድርጅት ፍቅራቸዉ በቀላሉ ምትክ የማይገኝላቸዉ፤ በወታደራዊ ችሎታቸዉም ሆነ በአጠቃላይ የትግል
ባህሪያቸዉ  የሁሉም አርአያ የነበሩ ጓዶች የተሰዉበት ጦርነት ነው፤ በመጽሐፌ እንደጠቀስኳቸዉ ከሁሉም የኢት
ይጵያዉያን ብሔሮችና ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች የመጡ፤ የእቢዮንና ህብስቱን የመሰሉ ጀግኖች ያጣንበትን
ዉጊያ ነዉ፤ ይህን ኦፐሬሽን ለመወሰንም የፓርቲዉ ከፍተኛ አመራር ልኡኮች አሁንም ከፍተኛ ሚና ተጫዉተዋ
ል፤ በወቅቱ ኢሕአፓ በዉስጣዊ ችግሮች ተውጥሮ ዉስጥ ለዉስጥ እየተብላላ፤ የጓዶች ሞራልና ዲስፒሊንም በተዳ
ከመበት ወቅት፤ ከጠላት ጋር የመዋጋትን ኦፐሬሽን ጋብ አድርጎ በቅድሚያ እራስን ማጠናከር ሲገባ፤ በሚገባ ባልተ
ጠና ኦፐሬሽን ጓዶችን ልኮ በእሳት መማገድ ባላስፈለገ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን በተለይም በአመራር ላይ የነበሩት እንደ
ህብስቱና የእቢዮ ያሉት ቆራጥ ጓዶች በጀግንነት ጠላትን ተጋፍጠዉ መስዋእትነትን ከፍለዋል፤ በዚህ ያልሆነና በሚገባ
ያልተጠና፤ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዘነ ዉጊያ ያንን ያክል ከባድ መስዋእትነት መክፈልና እነሱን የመሰሉ ምርጥ ጓዶች
ማጣታችን ግን የብዙ ጓዶችን የእኔንም ጨምሮ ሞራል የነካና ለረዥም ጊዜ ልባችን ያቃጠለ እንደነበር አጠያያቂ
አልነበረም።

በዚህ ዉጊያ ላይም ሽፈራዉ የእኔን ጀብዱ እያጋነንኩ የሌሎችን ጓዶች ግን እያንኳሰስኩ ከዚያም አልፎ ጭራሽ "የት
ግራይ ጓዶችን" ዝና ብቻ እየመረጥሁ እንደጻፍኩ አድርጎ ይዘልፈኛል፤ ይህን እንግዲህ ምን እላለሁ ፍርዱን ለአንባብ
ያንና በተለይም በህይወት ላሉ ጓዶች እተወዋለሁ፤ ከዚያ ግን አሁንም ሽፈራዉ ከትችቱ እንደተረዳሁት በዚህ ኦፐሬሽ
ን ያሳየሁትን የእኔን ጀግንነት በመጽሐፍህ ለምን አላካተትክልኝም የምትል ይመስላል፤ ጓድ ሽፈራዉ በቅድሚያ
እኔ በሚገባ እስከማስታዉሰዉ ድረስ አንተ እንኳን በከባድ መሳሪያ (በ RPG) ተኩሱን ልትከፍትልን ቀርቶ በዉጊ
ያዉ እሳት ዉስጥ እንዳልነበርክ ነዉ፤ ይህንም አሁን በህይወት ባሉ ጓዶች በወቅቱ መሪወች በነበሩም ጭምር ለማ
ጣራት ይቻላል፤ ዋናዉ ፍሬ ነገሩ ግን በሚገባ ቁልጭ አድርጌ የማስታዉሰዉ ያኔ ከባድ መሳሪያ (RPG) ይዞ የነበረ
ዉን ጓድ ነዉ፤ ይህም ጓድ አሁን የት እንዳለ ቦታዉን በትክክል አላቅም እንጅ በህይወት ተርፎ ከሀገር እንደወጣ ነ
ዉ፤ የጓዱ ስምም ብርሀኔ ይባላል (የአባቱን ስም አላስታዉስም)፤ ካስፈለገ እሱን አፈላልጎ ማጣራት ይቻላል።

አሁንም ዋናዉ ቁጭትህ ለምን የእኔን ጀብዱና ጀግንነት በዉቅሮ ጦርነት የሰራሁትን በመጽሐፍህ አልጻፍክም ብለ
ህ ከሆነ ይቅርታ አድርግልኝና በቅድሚያ ከአንተ በዉቅሮ ኦፐሬሽን በተለይ ትዝ የሚለኝና በህሊናየ የተቀረጸ ጀ
ግንነት አንድም የለም፤ በተጨማሪም እኔ አሁንም በትችትህ እንደጠቆምኸዉ ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለመ
ጥቀም ወይም ለማንቋሸሽ አለዚያም ዝና ለመገንባት ወይም ለማጣጣል አይደለም መጽሀፉን የጻፍኩት፤ አንተ
ህሊናህ ካልወቀሰህ የፈለግኸዉን መጥፎ ስምና ጥላሸት ብትቀባዉ ምንም ማድረግ አልችልም፤ ታሪክና ሀቅ ግ
ንጨርሰዉ  አይጠፉም፤  አንተ የምትላቸዉንም ሆነ ወይም እኔ በመጽሐፌ  ያካተትኳቸዉን ክስተቶች ዋና ዋና የሚያለያዩን
ን ነጥቦች ካስፈለገ እያጣሩ  ከጊዜ ጋር ማመሳከር ይቻላል።

## መ) ብአጠቃ ላይ የኢህሰን አመራር በሚመ ለከት፤

ሽፈራዉ የኢህሰን አመራር ወይም ሰራዊቱን የሕዝብ ሳይሆን የነጭ ሰራዊት እንደነበር አስመስሎ በመጽሐፉ ጽፎአ
ል ብሎ በትችቱ ያወግዘኛል፤ መቸም ገና በጮርቃ እድሜየ ህይወቴን ለሀገሬ ፍቅር በሚል አሳልፌ ሰጥቸ፤ የአቅ
ሜን ስንት ፈተናና መስዋእትነት የከፈልኩበትን ከእራሴ አብልጨ የምወደዉ የነበረዉን ድርጅትና ሰራዊት የነጭ

ሰራዊት ነበር የሚመስል ብየ ባወግዝ ሰራዊቱን ብቻ ሳይሆን የእኔን የእራሴንና የስንት ጀግኖች ጓዶቸን በቆ
ራጥነትየተሰዉትን ታሪክ ጭምር በአፈር እንደማዳፈን ይሆናል ብየ ነዉ የምቆጥረዉ፣ ሽፈራዉ ይህን ስትል
አፍክን እንዴት እንዳልያዘህም ይገርመኛል፣ የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር የሰራቸዉ በርካታ የፖለቲካና የወ
ታደራዊ ስትራቴጅ ስህተቶች ነበሩ ብየ ባምንም፣ የነጭ ሰራዊት ይመስል ነበር ብየ ግን አስቤዉም አልሜ
ዉም አላቅም፣ ይህን እንግዲህ ፍርዱን ለአንባብያን እተወዋለሁ፣ ምናልባትም ሽፈራዉ ከአየር ወለድ ስለመ
ጡ ጓዶች የጻፍኩትን ወደክፉ ተርጉሞ ከሆነ እንደዚያ የሚለዉ አሁንም ፍርዱን ለአንባብያን እተወዋለሁ፣ በቆራ
ጥነታቸዉ የበርካታ የኢህሰ ሰራዊት ጓዶች አብነትና አርአያ የነበሩትንና በኢትዮጵያ አየር ወለድም ዉስጥ እያሉ
ቢሆን ብርቅና ልዩ ታሪክ የነበራቸዉን ምርጥና ቆራጥ ጓዶች እነ ህብስቱን፣ ጌትነትንና አበጀን (ኮለኔል አለማየ
ሁ) የመሰሉትን በክፉ ስም ብጠራቸዉ ህሊናየንመዉቀስ ብቻ ሳይሆን ሳስበዉም በጣም ይረብሸኛል፣ ይህ የሽ
ፈራዉ ትችት ከሁሉም እርካሽ ስለሆነ በዚህ አል

ፈዋለሁ::

## ሠ) ጓዲት ድላይን በሚመለከት፣

መቸም የአሲምባ ፍቅር መጽሐፌን ለማጣጣልና፣ ስሜን ለማጉደፍ የተቀነባበረ ዘመቻ የተከፈተብኝ አርእስት
ቢኖርስለእኔና ድላይ የትግል ብቻ ሳይሆን የፍቅር ግንኙነት በጻፍኩት ላይ እንደሆነ እስካሁን ከቀረቡት
የአሉታ ትችቶች የሽፈራዉን ጨምሮ ለማየት ይቻላል፣ በጥቅም በመገዛት መጽሐፉ እንዲሸጥልኝ፣ የድላይን
የትግል ታሪክ ብቻሳይሆን የኢህሰንም ስም ጭምር እንዳጎደፍኩና ትልቅ ወይም እርካሽ ወንጀል እንደሰራሁ
ተደርጎ ለማቅረብ ተችወቹ ብዙ ሞክረዋል፣ ይህን ግን በትክክል ለማገናዘብ ወይም ፍርዱን ለመስጠት አሁን
ም ለአንባብያን እተወዋለሁ፣በመጽሐፌ ላይ ታሪኩን በትክክል ከማቅረብ አልፌ፣ በቆራጥነቷና በሀገር ፍቅር
ስሜቷ በጣም የማከብራትንና ከዚያም አልፎ በህይወቴ እስካለሁ ድረስ ትዝታዋንና ስእሏን ከህሊናየ የማላወጣ
ትን ብርቅ ጓዲት፣ ስሟን በክፉ አንስቻለሁ ወይም አነሳታለሁ የሚል ቅንጣት ያክል ስጋትም ሆነ እርካሽ ዐላማ
የለኝም፣ የዚህ አይነት ያዘቀጠ ባህሪም ኖሮኝ አያቅም፣ ለወደፊቱም ሊኖረኝ እንደማይችል በእራሴ እተማመናለሁ፣
ስለዚህ የሽፈራዉ ወይም የሌሎች እርካሽ ትችት መንፈሴን አይረብሸዉም፣ ሀቁን ከመናገርም ወደኋላ እልልም፣
ሀቁም በአጭሩ እንዲህ ነዉ::

አንባብያን በሚገባ ይረዱልኛል ብዬ እንደምገምተዉ የድላይን ቆራጥነትና፣ ከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት
ወይም ወታደራዊ ችሎታና ዲስፕሊን የሚያቃልል ነገር በመጽሐፌ ዉስጥ የተናገርኩት አንድም የለም፣ እን
ዲያዉም ሽፈራዉና መሰሎቹ ቅንነት በሌለዉ ሴራና ተንኮል ታሪኩን እያጣመሙ አቀረቡት እንጅ፣ እኔና ድ
ላይ ገና በወጣትነት እድሜአችን፣ የተፈጥሮ ስሜታችንና ሙቀታችን በሚግልበት ፈታኝ ዘመን፣ የአጋጣ
ሚና የአካባቢ ሁኔታውች በፈጠሩት ሳቢያና በትግል ጥንካሬአችን የጋራ ተሞክሮ በፈጠረው በጣም የመቀ
ራረብ ዝንባሌ ምክንያት፣ በተፈጥሮ የፍቅር ሀይል መሳባችን ጥፋት ሊሆን አይችልም ነበር፣ ለምን ቢሉ ይህ
የተፈጥሮ ህግ ነዉና፣ ያም ሆኖ ግን ወታደራዊ ዲስፕሊን ለመስበርና ድንበር ለማለፍ ባለመብቃታችን ያስመሰ
ግነናል እንጅ እኔንም ሆነ ድላይን ሊያስወቅስንይገባል ብየ አላምንም::

እኔን እዉነቱን ሆነ ብየ ለእርካሽ ጥቅም "መጽሐፌን ለማጣፈጥ" በሚል አጣምሜ እንዳቀረብኩት አድርጎ
መወንጀልም ተገቢ አልነበረም፣ ያኔ የገጠመንን ፈተናና ወይም የትግልና የተፈጥሮ ፍቅር ግጭትና ገጽታ
የምናቀዉ እኔና ድላይ ብቻ ነን፣ እኔ በእድል ከእሳት ተርፌ በእድሜ ቆይቸ፣ እሷ ግን እኔ ያገኘሁትን እ
ድል አጥታ መስዋትነት ብትከፍልም አሁንም ድረስ በጣም የምወዳትንና የማከብራትን ትዝታዋ በህሊናየ
የተቀረጸዉን፣ ቆራጥና ብርቅ የሁሉም ታጋዮች አርአያ የሆነች ጓዲት መጠቀሚያ አደርጋታለሁ ብሎ ማሰ
ብ እራሱ እኔን ብቻ ሳይሆን ይህን የሚተቹትንም ህሊና የሚፈታተንና የሚያስወቅስ የሚያስገምት ይ
መስለኛል፣ በእኔ ግምት እኔን ለማጥቃት ሲሉ ስሜት በሚቀሰቅስ እርካሽ ትችት ሁሉም የሚያ

ፈቅራትንና በህሊናዉ ትዝታ የሚያያትን የቆራጥ የኢሀሰ ጓዲቶች ሁሉ አርአያና ሞዴል የነበረችዉንና አሁን
ም በበርካታ ጓዶች ህሊና ህያዉ ሆና የምትኖረዉን የጓዲት ድላይን ስም መጠቀሚያ ያደረጉት እኔ ሳልሆን
እነሱ ናቸዉ ብየ በማመን ከልቤ አዝኛለሁ፡፡

ከዚያ በተረፈ ግን በኢሀሰ ዉስጥ ምንም አይነት የተፈጥሮ ፍቅር ወይም የወንድና ሴት ግንኙነት አልነበረም፣
ወይም ኢሕአሰን መናኞችና ቅዱሳን ታጋዮች የተሰለፉበት ሰራዊት አስመስሎ ማቅረብ አሁንም ታሪክን ማዛባት
ነዉ ብየ አምናለሁ፣ ኢህእሰ ከሰማይ የወረደ የቅዱሳን ሰራዊት ሳይሆን ከህብረተሰቡ አብራክ የወጡ ወጣቶች ገና
በትኩስ እድሜአቸዉ ወላጆቻቸዉንና ቤተሰቦቻቸዉን ጓደኞቻቸዉን እየተዉ ሀገራቸዉን ከግፍና ከድህነት ነ
ጻ ለማውጣት ወደትግል መስክ የገቡበት ወታደራዊ ድርጅት እንደነበር ግልጽ ነዉ፣ ገና በወጣትነታቸዉ ሊያ
ገኙ የሚችሉአቸዉን የፍቅር አይነቶች በሙሉ እየጓጉ እያሉ፣ ሁሉንም ሳያዩና ሳይጠግቡ ጣል አድርገዉ ስለወጡ፣ በ
ሰራዊቱ ዉስጥ እያሉ ያንን ወርቃማየወጣትነት ጊዜ ለመርሳት እራሱ አንድ ፈታኝ የዉስጥ ትግል እንደነሚሆ
ንባቸዉም ለመገመት አያስቸግርም፣ ይህአይነት ችግርም በኢሐፓ/ስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፣ በሁሉም የትጥ
ቅ ትግል ተዋጊወች ወይም ሰራዊቶች፣ በኢትዮጵያ ዉስጥ በነበሩ ብቻ ሳይሆን በዐለም ዙሪያ ባሉ ወይም በነበሩ ሁ
ሉ የሚከሰት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህም የተነሳ በኢሀሰ ዉስጥ የወንድና ሴት ግንኙነት ወይም በፍቅር መተሳሰርና የወታደራዊ ድንበር ማለፍ በጥ
ብቅ የተከለከለ መሆኑን እያወቁ፣ በርካታ ጓዶች ህጉን በድብቅ በመጣሳቸው ሲነቃባቸዉና ሲታወቅባቸዉ እዳ እየገ
ቡ ቅጣት የደረሰባቸዉና፣ ከሰራዊቱ እስከመባረር ድረስ የደረሱ በርካታ ነበሩ፣ ይህ ሀቅ ሆኖ እያለ ሽፈራዉና ሌሎ
ችም የመጽሀፌ ተቿወች ግን ይህን ሀቅ በመሸፋፈን ችግሩ እንዳልነበር እኔም ይህን መጥቀሴ የሚያሳፍርና
ሐሰት እንደሆነ እያስመሰሉ በተከታታይ የዘለፉ ዘመቻ ሲያቀርቡብኝ ቆይተዋል፡፡

በድላይና እኔ የነበረዉን የፍቅር ግንኙነትም እንዳላዩ እያዩ የሚታዘቡ የነበሩ ጥቂት ጓዶች ከሜዳ ከወጣን በሁዋላ
የነገሩኝ አሉ፣ ይባርካቸዉና ያን አይተዉ ለአመራሮቻችን አልተናገሩም እንጅ ቢከሱን ኖሮ ሁለታችንም
ምን አይነትቅጣትና ሀፍረት ይደርስብን እንደነበር ለመገመት አያዳግትም፣ ድላይና እኔ ግን ምንም
እንኳን በነበርንበት ሁኔታ ያንን በጥብቅ የተከለከለ ግንኙነት ለመፈጸም አመች ሁኔታወች የተፈጠሩልን ልዩ
አጋጣሚወች የነበሩ ቢሆንም፣ የትግላችን ዐላማ በማስቀደምና የሰራዊቱን ዲስፕሊን በማክበር ፈተናዉን ተቋቁ
መን ለማለፍ በቅተናል፣ ይህ ደግሞ ሊያስመሰግነን ይገባል እንጅ እኔንም ሆነ እሷን ሊያስወግዘን አይችልም፣ ከዚ
ያም አልፎ ግን በኢሀሰ ዉስጥ ይህ አስነዋሪ ነገር ፈጽሞ አልነበረም፣ ድላይንም በሚገባ እናቃታለን፣ አታደርገዉ
ም፣ ፍቅር ሊይዛትም ሆነ በዚያዉ ሳቢያምበስህተት ጥይትም ሊባረቅባት አይችልም እያሉ መፎከሩ ዋጋ የሌለዉ
በእኔ ላይ የተጠነሰሰ እርካሽ ሴራና ዘለፋና፣ በአሲምባ ፍቅር መጽሐፌም ላይ ጥርጣሬ እንዲሰፍንና አንባብያንም
እንዲደናገሩ ሆነ ተብሎ የተጎነጎነና የተቀነባበረ ዘመቻ ስለሆነ ፍሬ ቢስ ነዉ በሚል ፍርዱን ለአንባብያንንና በህይ
ወት ላሉ ጓዶች በመተዉ ይህን ትችት በዚህ አልፈዋልሁ፡፡

## ረ) ደብተራዉ (ፀጋየ ገብረመድህንን በሚመለከት)፤

ደብተራዉን በሚመለከት ሽፈራዉ ያቀረበዉ ትችት አሁንም እራሱ በመሰለዉ መንገድ ለዘለፋዉና የ
ኔን ስም ለማጥፋት በሚመች መልክ እየተረጎመ ነዉ፣ ይህን ለማድረግ ሲሞክርም ህሊናዉ በጥላቻ ስለ
ተበረዘ ቀላሉን ነገር እንኳን ለማየት አልቻለም፣ ይኸዉም አንባቢ ትችቱን እንደሚያየዉ ሽፈራዉ በአንድ በኩል
የደብተራዉ ሽጉጡ አልጠፋም ነበር፣ ወደከተማ ለስራ ተላከ እንጅ ይለንና መልሶ ደግሞ ሽጉጡ ጠፋ የተባለዉ
"ጓድ አማኑኤል እስከዛሬ ካላወቀዉ ወደ ከተማ ሲላኩ ጓዶችን ለመሸፈን ነበር ይላሉ" ይለናል፣ ጓድ ሽፈራዉ እ
ስኪ አሁን እረጋ ብለህ አጢነዉ፣ አንደኛ የጓድ ደብተራዉ በውቅቱ ሽጉጡ ጠፋ ተብሎ መነገሩን አንተም
ያመንክበትን ታሪክ በመጽሐፌ ዉስጥ በማካተቴ ምንድን ነዉ ጥፋቱ?

ከዚያ በተረፈ ግን እኔ ደብተራዉን አንተ አጣመህ እንደተረጎምኸዉና እንደምታስበዉ በአሲምባ ፍቅር መጽ ሐፌ "አንባገነን፣ ጨቋኝ የሚይከሰስ ፍጹም አለቃ አድረጌ ለማቅረብ ፍላጎቴም አልነበረም አላደረግሁትምም፣ አንተ ብቻሳትሆን ለሌሎችም አንባብያን ይችን የሽጉጡን መጥፋት ብቻ ታሪክ ቆንጽለዉ በመዉሰድ እኔ ደ ብተራዉን አንተእንደምትለዉ አንባገነንና ጨቋኝ ብየዋለሁ ብለዉ የሚተረጉሙና የሚያስቡ ከሆነ ምንም ማድረግ አልችልም ከማዘን በስተቀር፣ እኔ ድርጊቱን እንዳለ እንደነበር ነዉ ያቀረብኩት፣ እንዲያዉም ለእኔ ያ ኔ የተሰማኝ ስሜት በሙሉ ልንገርህና ደብተራዉ "አማኑኤል ሀቅን መናገር ሁልጊዜም ያዋጣል ማለት አይደለም " ሲለኝ እኔን እንደ ልጁ ስለሚያየኝ በማቅረብ የአባትነት ምክር እንደሰጠኝ እንጅ ሊያስፈራራኝ ነዉ ብየ አ ላመንኩም፣ ደብተራዉም ስለወደደኝ እንጅቢፈልግ ኖሮ በነበረዉ ስልጣን በድፍረት ፊት ለፊቱ ሄጀ ለምን አንተ ሽጉጥህን ስትጥል አልተቀጣህም ስለዉ እንዳይደገመኝ አድርጎ ማስፈራራት ብቻ ሳይሆን ከባድ ማስ ጠንቀቂያ በሰጠኝ ወይም በቀጣኝ ነበር፣ እኔም እራሴ ቢሆን ደብተራዉን አንባገነን ነዉ ብየ ብገምት ኖሮ ደፍ ሬ ሄጀ ፊት ለፊት እንደዚያ አይነት ጥያቄ ባልጠየቅሁትም ነበር፣ስለዚህ ይህን እርካሽ ትችትህን ም እሁንም ፍር ዱን ለአንባብያን ትቸ በዚህ አልፈዋለሁ::

## ሰ) ስለነበለት ጦርነት (ሀይል 74)፣

የሽፈራዉን ሽር የሞላበትና ጠማማ ትችት ዋና ምክንያት ምናልባትም ስለዚህ ጦርነት በአሲምባ ፍቅርመጽሐፌ ዉስጥ የጻፍኩትን ጠምዝዞ ያቀረበዉ ምስክር ሊሆን ይችላል፣ ለእኩይ ዐላማዉና አሁ ንም የዘረኝነትና የትምክህት መርዝ የተጠናወተዉ መሆኑን ማሳያ ከዚህ የተሻለ ትችት የሚገኝ አይ መስለኝም፣ ይህ ሁሉ ዳንስና መሽከረከር አፍ አዉጥቶ በድፍረት መናገር ወኔ እያጣ እንጅ ሽፈራዉ እኔን አማ ኑኤል ከድሮዉ ገና ኢህአሰ ዉስጥ እያለ ጀምሮ ልክ እንደሌሎች "የትግራይ ጓዶች" "የወያኔ" ወኪል ወይም ሰላይ ነበር ለማለት ነዉ ይህን ሁሉ የሚዘልፈኝ፣ ለዚህም እርካሽ ዘለፋዉ ምናልባት ምሳሌ ሊሆን የሚችል በአን ድ በኩል እኔን የኢሐፓን ታሪክ በእሁኑ መነጸር እያየህ በረዝከዉ እያለ እየወነጀለ፣ እሱ በዚያዉ ወጥመድ ዉ ስጥ ገብቶ መዛቀጡና መዉጫ ማጣቱነዉ፣ ሽፈራዉ እንደሚለዉም፣

"ከሰላሳ አመት በፊት የነበረዉን ትግል ዝዞ በአሁኑ አመለካከት በርዞ፣ ሰርዞ፣ አጨማልቆ ማቅረብ ግን በታሪክ አስጠያቂ ያደርጋል:: የአሁኑን የፖለቲካ አመለካከት በድሮ ታሪክ ላይ ለማንፀባረቅ መሞከር ግን ተገቢ አይደለም:: ያስጠይቃል የታሪክ ተወቃሽ ያ ደርጋል::"

ይህን በጣም የበሰለና አስተዋይ የሚያሰኝ ምክር እየሰጠ ግን ሽፈራዉ እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የኢሀሰ "የትግራይ ጓዶች" እያለ የሚጠራቸዉን ጓዶችን ስም በሚያጠፋ መርዝ እየለወሰ አሁንም የወያኔ አባል ነበሩ ለማለት ነዉ ዐላማዉ፣ እኔንም ወያኔን "ለማስደሰት" ነዉ ኢህአፓ/ሰ ን እያወገዘ የአሲምባ ፍቅር መጽሐፉን የ ጻፈዉ እያለ ያወግዘኛል፣ ለምሳሌ ስለነበለት ጦርነት በመጽሐፌ የጻፍኩትን ሲተች ሽፈራዉ እንዲህ ይላል፣

አማኑኤል "ከአንድ ጋንታ አራት ብቻ እስኪቀሩ ተደመሰሱ የሚለን ለምን ይሆን? በመጽሀፉ የከተተዉ የትግራይ ልጆች ጀግንነት ፣ የወያኔን ጥንካሬ ሊያወሳልን ብሎ ወይም አስቦ ይሆን? ስለነበለቱ ጦርነት በቦታዉ የነበሩ ቢያወሩ ሀቁ እንዴት በወጣ ነበር::" ይላል::

ሽፈራዉ እኔ ስለነበለቱ ጦርነት የጻፍኩት ልክ አይደለም ካልክ ምናለበት ትንሽ ሰፋ አድርገህ በትችትህ ስለጦር ነቱ በገለጽክልን ነበር? ለምን እኔን ለመዝለፍ ተጠቅመህ በአጭር ቀጨኸዉሳ? መቸም ከዚህ ከፍተኛ የተጠና ወተህ ክፉ ጠባብና የዘረኝነት በሽታ ከጓዶችም (በተደጋጋሚ "የትግራይ ተወላጆች ወይም የትግራይ ጓዶ ች እያልህ ከምትጠራቸዉ) ጥላቻ ተላቀህ እንዳይህ እመኝልሀለሁ! ሌላ ምንም አልልም፣ አሁንም ፍርዱን ለ አንባብያንና በህይወት ላሉ የሁለታችንም ታሪክ አመዛዝነዉ ሊፈርዱ ለሚችሉ ሀቀኛ ጓዶች እተወዋለሁ::

## ሸ) የአማኑአል ኢሕአሰን ክ ህደት፤

ይህን የሸፈራዉ ትችት በሚመለከት ከላይ በ 3ሀ ክፍል ሰፋ አድርጌ ስለመለለስኩት እዚህ ላይ አጠር አድርጌ በጥቅሉ መልስ በመስጠት  ወደፊት እዘልቃለሁ፤ እንደተለመደዉ ሸፈራዉ እርካሽ ዘለፋዉን እዚህም ላይ ሊያ ወርድብኝና ስሜን ሊያጠፉኝ ብዙ ሞክሮአል፤ ግን እኔም ልንገርህና ሞራሌ ነቅነቅ አይልም፤ የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍም በአንባቢያን ያለዉ ተቀባይነት በሸፈራዉም ሆነ በሌሎች እርካሽ ዘለፋና ቅንነት የጎደለዉ ትችት ይቀንስ ይሆናል የሚል ስጋት የለኝም፤ ሸፈራዉ እዚህም ላይ እንዲህ ይላል፤

"አማኑኤል ከሰራዊቱ ሲወጣ ከሌሎች ሁለት የትግራይ ጓዶች ጋር በመሆን በጦርነቱ መሀል ጓዶችንና ጓዲቶችን አስተኝቶ መሳሪያ በመስረቅ ከድቶ ወደ ኤርትራ በመኮብለሉ ብዙ ባያስገርመኝም የራሱን ክህደት እንደ ትክክለኛ አመለካከት ሊያስረዳን መሞከሩ የበለ ጠ አሳዝኖኛል" ይላል።

ጓድ ሸፈራዉ የለም አንተማ ወደ ኤርትራ ስትገባ እየፎከርክ አገር አዉቆህ ፀሀይ ሙቆህ ነዉ የገባኸው! አ ታፍርምይህን ስትል! በስንት መቶ የሚቆጠር ሰራዊት ብረቱን አስወርዶ አንገቱን አስደፍቶ እየመራ የገባዉ ን የኢሐፓፓርቲ የከፈተኛ አመራር መዉቀስ ትተህ እኔንና "የትግራይ ጓዶችን" የታሪክ መወቀሻ ማምለ ጫ (scapegoat)ለማድረግ መከራህን ታያለህ! በል እስኪ በአንተ መጽሀፍ ትክክለኛዉን ታሪክ ስትጽፈዉ ለማን በበ በጉጉት እንጠብቃለን!

ሸፈራዉ ቀጥሎም በዚህ ትችት ላይ አሁንም ዘረኘነትና የሕዝብ ጥላቻ በተካበ አነጋገር እንዲህ ይላል፤

"አማኑአል በመጽሐፉ እንዳቀረበዉ የትግሬ ልጆች በየጊዜዉ በመመካከር እንደዚህ ያለ የክህደት ተግባር መፈጸማቸዉ በህብረ ብሄረሰብነቱ የሚያምነዉን ቆራጥ ትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ጀግኖች የመስዋትነት ታሪክ ላይ
ጥላሸት መቀባት ነዉ እላለሁ።"

ጓድ ሸፈራዉ ይህ መቸም የአዞ እንባ ነዉ እላለሁ፤ አሁንም ፍርዱን ለአንባቢያን እተወዋለሁ፤ ገና የኢሀሰ ሰ ራዊት ሲፈጠር ጀምሮ ከህወሀት ተጋዳዮች ሳይቀር የሚሰነዘርባቸዉን ጥቃት ግንባር ቀደም በመሆን በቆራ ጥነት በመጋፈጥ፤ ከዚያም አልፎ ከደርግ ጦር ጋርም ሆነ ከጸረ ህዝብ ሚሊሽያ ጋር በቆራጥነት ፊት እየቀ ደሙ እየተፋለሙ ለድርጅታቸዉና ሰራዊታቸዉ ለኢህአፓ/ሰ ለሀገራቸዉም ፍቅር በዉድ ህይወታቸዉ የከ ፈሉትንና ከባድ መስዋእትየከፈሉትን የትግራይ ተወላጅ ጓዶች ከሀዲና ደካሞች የወያኔ ወኪሎች ነበሩ እያ ልክ ሳትሳቀቅ ህሊናህ ሳይወቅስህ አፍክን ሞልተህ እየዘለፍክ ዞረህ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ተቆርቋሪ መስለህ ል ትቀርብ ትሞክራለህ! ይህን ሁለት ም ላስ ምን እላለሁ? አሁንም ፍርዱን ለአንባቢያንና በህይወት ላሉ ጓዶች ከ መተዉ በስተቀር።

በነገራችን ላይ እያወቅህ መናገር ያልፈለግኸዉን ታሪክ ላስታዉስህ፤ የህወሀት ተጋዳዮች በኢሀሰ ጦር ላይ ጥ ቃት ሲፈጽሙ ገና ከጅምሩ እራሳችን እንከላከል ግምኛ እየተጠቃን ነዉ እያሉ የኢሀሰ ጓዶች በተለይም የሰራ ዊቱ አመራሮች ኡኡ እያሉ ለፓርቲዉ ስሞታ ሲያቀርቡና ሲጮሁ፤ የለም ተዉ! የህወሀትን ተጋዳዮች መንካት የለባችሁም እያለ የሚከለክለው የፓርቲዉ የማእከላዊ ኮሚቴ ከፍተኛ አመራር ወይም እራሱን ልኡክ ብሎ ይጠራ የነበረዉ ቡድን እንደነበር የአደባባይ ምስጢር እንደነበር የሚጠፋህ አይመስለኝም፤ በዚህ የትንቅንቅ ወቅትም በህ ወሀት ተጋዳዮች አነሳሽነት በሚፈጠሩት ግጭቶችና በኢሀሰ ጓዶችና ደጋፊወች ላይ በሚሰነዘሩት ጥቃቶች ሰ በብ ጥቂት የማይባሉ የትግራይ ተወላጅ የኢሀሰ ጓዶችና የሚሊሽያ አባሎች ብዙ ጉዳት መስዋትነት ሳይቀር እን ደደረሰባቸዉ እያወቅህ "የትግራይ ጓዶች" ከሀዲና የወያኔ ወኪሎች ነበሩ ብሎ መወንጀል የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆ ን በታሪክ ላይ ደባ መፈጸም ነዉ ብየ አምናለሁ፤

በመጨረሻም በተራ ቁጥር 8 ላይ ላቀረብከዉ ዉሸት የሞላዉ ትችት መልስ ልሰጥህ እፈልጋለሁ፤ አማኑኤል የእኔንና "በትግራይ ጓዶች" ላይ "በወያኔና ኢህአፓ" ይደርስብን የነበረዉን ስቃይ በመጽሐፍ መጻፍ እፈል ጋለሁ ብሎ ነግሮኛል ትልና ስለዚህም "እዉነቱን ነዉ በመጽሀፉ ዉስጥ የጠቀሳቸው አብዛኞቹ የትግ ራይ ልጆችን ጀግንነት ነዉ"ትላለህ! መቸም ለአንተ ለታማኝ ጓደኛየ ሳላቀው ስንት ምስጢር ነግሬሀለሁ እባ ክህ! ይገርማል! ይህን ካልኩህ ታዲያ ምነዉ በመጽሐፌ ዉስጥ "በእኛ በትግራይ ተወላጆች በወያኔና በኢሐፓ የደረሰብንን በደል" በሚገባ ያልጻፍኩት? ይህን ዉሸትክን ለማጣራት መቸም ለአንባቢ እተወዋለሁ ሌላ ምን እላለሁ!

ይሁን እንጅ ዉሸትክን ንቄ ትቸ በአንድ በኩል በዚህ ትችትህ አመስግንሀለሁ፤ የጠቀስከዉ "የደካማና ከሀዲ የ ትግራይ ልጆችን" ታሪክ ብቻ ነዉ አለማለትህ ገረመኝ! ማናልባት ሳታስበዉ ሳት ብሎህ ይሆን በመጽሐፉ የ ጻፈዉ በሙሉ እየመረጠ የትግራይ ጓዶችን ጀግንነት ብቻ ነዉ ብለህ የከሰስከኝ፤ ወይስ ሙሉ በሙሉ ለመ ዋሸት ተምታታብህ፤ ምነዉ "የትግራይ ጓዶችን ወይም ተወላጆችን" ሳት ብሎህ ጀግና ብለህ ጠራህ? በነገ ራችን ላይ ይህን እርካሽ ዘለፋህን አሁንም ለአንባብያን ብቻ ሳይሆን በህይወት ላሉ ጓዶች ፍርዱን እንዲሰጡ እተወዋለሁ።

በአሲምባ መጽሐፍ ላይ እኔ ባሳላፍኳቸዉ ዉጊያወች በጀግንነት የተሳተፉ ግን ደግሞ አንተ እንደምትለዉ "የትግራይ ተወላጆች" ያልሆኑ ሆነ ብየ መርጬ የተዉኳቸዉ ካሉ ህሊናየና የእነሱ ህይወትና ታሪክ ይፋረዱኝ! ሌላ ምን እላለሁ! እኔ በተሳተፍኩባቸዉ ጦርነቶች በሙሉ አንተ እንደምተልዘፈኝ እያወቅሁ "የትግራይ ጓዶችን" ጀግንነት ብቻ እየጠቀስኩ ከሌላ ብሔር የመጡትን ጀግና ጓዶች ግን ሆነ ብየ ሳልጠቅስ አልፌ ከሆነ ሌ ሎች አንባብያን ብቻ ሳይሆኑ በህይወት ያሉ ጓዶች ይፋረዱኝ፤ ሌላ ምን እላለሁ፤ ከዚያ በተረፈ ግን እኔን ለምን እንደ ጀግና አልጠቀስከኝም ብለህ ከሆነ በኩርፊያ የምትዘልፈኝ ይቅርታ አድርግልኝና የአንተ ጀግንነትም ሆነ የታሪክ ዝና በምንም መንገድ ከጓድ ሀብስቱ፤ ጓድ የእቢዮ፤ ጓድ ጌትነትና ከሌሎችም በአሲምባ ፍቅር ዉስጥ ከጠቀስኳቸዉ ቆራጥና እዉነተኛ እርአያ የሆኑ ክቡር ህይወታቸዉን ለሀገራቸዉና ለድርጅታቸዉ ዐላማ አሳል ፈዉ ከሰጡና ከባድ መስዋእትነት ከከፈሉ ጋር ላስገባህ አልችልም፤ እኔም እራሴ ቢሆን በጀግንነቴ ከእነሱ እኩል ነኝ ብየ አስቤም አልሜም አላቅም።

በመጨረሻም ሽፈራዉ ከዚህ ትችት ጋር አያይዞ በተራ ቁጥር 8 ላይ አኔ ታጋይ መለስን ስለማግኘቴ በአሲ ምባ ፍቅር ላይ የጻፍኩትን በሚመለከት እንዲህ ይላል፤

"ይባስ ብሎ ደግሞ ለአንድ ቀን ያየዉን (መለስ ዜናዊ) ስለርማግኘቱና ስለማየቱ ጥርጣሬ ቢኖረኝም፤ አገኘሁት ብሎ ሊስለዉ ሊቀባዉ፤ አሁን የሚፈልገዉ (አሲምባ ፍቅር በገጽ 161-162) አሁን ከመለስ ራእይ ጋር መግጠሙ

ን በግልጽ ያሳያል። ገና በነሐገራዊ ዘመን፤ ገና ወያኔ እንጭጭ በነበረበት ጊዜ መለስ ዜናዊ አዋቂ፤ አስተዋይ፤ መጽሀፍ የሚያነብ ረጋ ያለ ብስል ነበር ይለናል።"

ጓድ ሽፈራዉ መቸም ለእዚህ መልስ ምን እንደምሰጥህ ግራ ይገባኛል፤ ለምን ቢሉ የእኔን እሱን ማግኘት መ ጠራጠርክን እንተወዉና አሁንም እንኳን ከዚህ ዐለም በሞት ተለይቶ ለመለስ ያለህን ከፍተኛ ጥላቻ ለመግለ ጽ ያስገባኸዉ እርካሽ ትችት እንጅ ሌላ እንዳልሆነ ግልጽ ስለሆነ ፍርዱን ለአንባብያን እተወዋለሁ፤ መለስን ማግኘቱን እጠራጠራለሁ የምትለዉም ተልካሻ ዘለፋ ነዉ፤ ትችትም አይደለም፤ እሱን ብቻ ሳይሆን ብዙ በመጽሐፉ ላይ ያሉትንም እዉነተኛ ታሪኮች ከመጠራጠርም አልፈህ እያጣመምክ ለማቅረብ ስለጣርክ ይ ህም ብዙ አይገርመኝም።

## ማጠቃለያ ፤

ከጓድ ሽፈራዉ ጋር እርግጥ ቀላል የማይባሉ የትግል ፈተናወችን አብረን አሳልፈናል፤ በእሳትም ዉስጥ አብረን ተ
ማግደናል፤ የአሲምባ ፍቅርን ለመፃፍ ላይ ታች ስልም እሱም እንደበርካታ ጓዶች የተቻለዉን ምክርና መረጃወች
ን ለግሶኛል፤ እንኳን ሌላ መጽሐፉ ወጥቶ ለሽያጭ ተዘርግቶ እያለም እየደወለ እኔም አልፎ አልፎ እየደወልኩለ
ት ምክር አካፍሎኛል፤ እሱ ብቻ አይደለም በጓደኝነትም በመቅረብ ይጠቅማል የሚለዉን ምስጢር ሁሉ አካፍሎኛል፤
ለምሳሌ በአሲምባ ፍቅር ላይ ያልሆነ ትችት ወይም አሉታ የሞላበትና ቅንነት የጎደለዉ የመሰለዉን ትችት ገና በይፋ
በዌብሳይቶች ከመዉጣቱ በፊት ሁሉ እነእገሌ ያልሆነ ዘለፋ ሊያወጡብህ ነዉና ተዘጋጅተህ ጠብቅ፤ ተጠንቀቅ፤ ከምን
ም ግን አትቁጠራቸዉ ሀቁን ስለማይናገሩ የትም አይደርሱም እያለ ሁሉ መክሮኛል፤ እኔም ከፈለጉ ያዉጡ መብ
ታቸዉ ነዉ፤ ዋናዉ መጽሀፌን ማንበባቸዉ ጥሩ ነዉ፤ በመጽሐፉ የሚቀርቡት ሁሉ ትችቶች ግን ሁሉም እኔን የ
ሚደግፉ ይሆናሉ የሚል የተሳሳተ ግምት የለኝም ብየ የጓደኝነት ምክሩን ግን አመስግኘ ተቀብየዋለሁ፡፡

ጥቂት ቆይቶ ግን ሙሉ ዙሪያ ቀኝ ሁዋላ ፊቱን ወደእኔ አዞሮ በድንገት ዘመቻ ሲከፍትብኝ እዉነቱን ለመናገር ከማስገ
ረም አልፎ እረብሾኝም ነበር፤ እዉነትም አባቶቻችን "ሰዉን ማመን ቀብሮ ነዉ" የሚሉትን አባባል ድሮ የማላምንበ
ትን አሁን ለማመን የጠየቅሁበትና የተቃረብኩበት ስአትም ነበር ብል ከእዉነት የራቀ አይሆንም፤ የሽፈራዉ ባ
ህሪ በጣም የገረመኝ ደግሞ ሌሎች ሊያቅርቡብህ ነዉና ተዘጋጅ ብሎ የመከረኝን ዘለፋና ዉሸት የሞላዉ ትችት በሙሉ
እራሱ በበለጠ አቀነባብሮ ማቅረቡ ነዉ፡፡

ይህን ባህሪ እንግዲህ ምንም መግለጽ አልችልም፤ ዋናዉ ነገር በቅንነት የማቀዉን የማስታዉሰዉን በሙሉ በትግል
የወደቁ የጀግናና ቆራጥ ኢህአሰ ጓዶቻችን ታሪክ ለማስታወስና ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣዉ ትዉልድ ለማበርከት
የአቅሜን ሞክሬአለሁ፤ ይህን የአሲምባ ፍቅር መጽሐፍ ሳበረክት ግን ሌሎችንም በተለይም በትግሉ ብዙ ተሞክሮ
ያላቸዉንና ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ለመጻፍ ችሎታ አላቸዉ ብየ የምገምታቸዉንና በትግል ታሪካቸዉም የማከብራ
ቸዉን፤ አሁን በህይወት ያሉ ጓዶችን በሰራዊቱ አመራር ሀላፊነት ላይ የነበሩትን ጨምሮ መጽሐፌ ለማነቃቃት
ይረዳ ይሆናል የሚልም እምነትና ተስፋ ይዠ ነዉ የጻፍኩት፤ ወድቆና ተረስቶ ለ40 አመት ያክል የኖረዉ በ
ተለይም የኢህሰ (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ሰራዊት) ታሪክም እንዲወጣና ሁሉም እንዲያዉቀዉ ያበረታታል
በሚል ነዉ ለአንባብያን የአሲምባ ፍቅርን ያቀረብኩት፡፡

ይህ መጽሀፍ የአሲምባ ፍቅርም ሙሉ በሙሉ ስህተት የለዉም ብየ እራሴን አላሞካሽም፤ ለወደፊቱም የእኔን ብቻ
ሳይሆን በትግል የወደቁትን ታሪክ ሳያዛባና ሳያጣምም ወይም ለፖለቲካም ሆነ ለሌላ ጥቅምና ዐላማ መጠቀሚያ
ሳያደርግ በመጽሐፉ ላይ በቅንነት የሚቀርብልኝን ትችት በደስታና በቅንነት ለመቀበልና አእምሮየን ክፍት አድ
ርጌ ስህተት ከተገኘብኝ ለመታረምና ከስህተቴ ለመማር እንደምጠባበቅ ለአንባብያኖቸ ከልቤ ልገልፅ እወዳለ
ሁ፡፡

አመሰግናለሁ

ካህሳይ እብርሀ (አማኑኤል)

ሕዳር 2006 (**October** 2013)